መልእክት ሦስት

## እንደ የሰው ልጅ በወርቃማዎቹ መቅረዞች መካከል የሚመላለሰው ክርስቶስ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 1፥9—2፥1

1. **እንደ የሰው ልጅ በወርቃማዎቹ መቅረዞች መካከል የሚመላለሰውን የክርስቶስን ራእይ እናይ ዘንድ፣ በኢየሱስ መከራ፣ መንግሥት እና ትእግሥት እንደሚካፈሉ በቤተ ክርስቲያን መቆሚያ ስፍራ ላይ በመንፈሳቸው የሆኑ የጌታ ድል ነሺ መልእክተኞች መሆን አለብን—ራእ. 1፥9-13፣ 20፦**
   - ሀ. በቀደሙ ጊዜያት የነበረው የአብያተ ክርስቲያናት ተግባራዊ ልምምድ ለአንድ ከተማ አንዲት ቤተ ክርስቲያን የመኖሯ ተግባራዊ ልምምድ ነበር፤ በየትኛውም ከተማ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን በላይ አልነበረም—ሐዋ. 8፥1፤ 13፥1፤ ራእ. 1፥11።
   - ለ. በእውነተኛው የአንድነት መቆሚያ ስፍራ፣ እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ የመሰብሰባችን አራት መለያ ባሕርያት አሉ—ተዛ. ዘዳ. 12፥5፦
     1. መጀመሪያ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁልጊዜ አንድ መሆን አለባቸው፤ በመካከላቸው ክፍፍሎች ሊኖሩ አይገባም—መዝ. 133፤ ዮሐ. 17፥11፣ 21-23፤ 1 ቆሮ. 1፥10፤ ኤፌ. 4፥3።
     2. ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊሰበሰቡበት የሚገባው ልዩና ብቸኛው ስም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ የዚህም ስም እውነታ መንፈስ ነው፤ በሌላ ስም መሰየም ዲኖሚኔሽን መሆን፣ መከፋፈል ነው፤ ይህ መንፈሳዊ ግልሙትና ነው—ማቴ. 18፥20፤ 1 ቆሮ. 1፥12-13፤ 12፥3።
     3. ሦስተኛ፣ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መኖሪ ስፍራ፣ የእርሱ ማደሪያ ስፍራ ልዩ በሆነ መንገድ የሚገኘው በመንፈሳችን ውስጥ ነው፣ ማለትም፣ በተዋሐደው መንፈሳችን፣ ዳግም በተወለደውና መለኮታዊው መንፈስ ባደረበት የሰው መንፈሳችን ውስጥ ነው፤ እግዚአብሔርን ለማምለክ ስንሰበሰብ፣ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስና ሁሉንም ነገር በመንፈሳችን ማድረግ አለብን—ዮሐ. 3፥6፤ ሮሜ 8፥16፤ 2 ጢሞ. 4፥22፤ ኤፌ. 2፥22፤ ዮሐ. 4፥24፤ ራእ. 1፥10፤ 1 ቆሮ. 14፥15።
     4. አራተኛ፣ እግዚአብሔርን ስናመልክ ሥጋን፣ እኔነትን እና ተፈጥሮአዊ ሕይወትን በመግፋት እና በክርስቶስ እና በክርስቶስ ብቻ እግዚአብሔርን በማምለክ (ማቴ. 16፥24፤ ገላ. 2፥20) በመሠዊያው እንደተመለከተው (ዘዳ. 12፥5-6፣ 27) የክርስቶስ መስቀል እውነተኛ ትግበራ ሊኖረን ይገባል።
   - ሐ. በኢየሱስ መከራ ተካፋዮች ነን፦
     1. *በኢየሱስ* ማለት የናዝሬቱን ኢየሱስን እየተከተልን ሳለ መከራን ለመቀበል የተትረፈረፈ ጥንካሬ ያለው መንፈስ በሆነው በውስጥ በሚኖረው በኢየሱስ መንፈስ መከራንና ስደትን እየተቀበልን ነው ማለት ነው—ሐዋ. 16፥6-7።
     2. ዛሬ መከራን እየተቀበልን ሳለ፣ ጌታ ኢየሱስ በእኛ ውስጥ እና ከእኛ ጋር መከራን እየተቀበለ ነው—9፥4-5፤ ዕብ. 13፥13።
     3. ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው በብዙ መከራ ነው—ሐዋ. 14፥22።
     4. በትንሣኤው ኃይል፣ በመከራዎቹ መሳተፍ እና የእርሱን ሞት በመምሰል የተሰቀለን ሕይወት መኖር እንድንችል እየተደረግን ነው—ፊልጵ. 3፥10፤ ቆላ. 1፥24፤ መኃ. 2፥8-9፣ 14።
     5. የነፍስ ሕይወታችንን እስከ ሞት ድረስ እንኳ መውደድ የለብንም፤ ስለ ወንድሞቻችንም ሕይወታችንን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባል—ራእ. 12፥11፤ 1 ዮሐ. 3፥16።
   - መ. በኢየሱስ መንግሥት ተካፋዮች ነን፦
     1. መንግሥቱ ታማኝ የሆኑ አማኞች በሕይወት ለሆነው እድገታቸው እና በሕይወት ለሆነው መለወጣቸው የሚኖሩበት የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ነው—ማቴ. 16፥18-19፤ ሮሜ 14፥17፤ 1 ቆሮ. 3፥7፤ 2 ቆሮ. 3፥18።
     2. የመንግሥቱን ሕይወት በተግባር ለመለማመድ፣ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርን እና ሰላምን መከታተል ያስፈልገናል—2 ጢሞ. 2፥22።
     3. የመንግሥቱን ሕይወት በተግባር ለመለማመድ፣ ኃጢአት ያደረጉ ወንድሞችን ለመመለስ ግድ ልንሰኝላቸው ያስፈልገናል—ማቴ. 18፥15-22።
   - ሠ. በኢየሱስ ትእግሥት ተካፋዮች ነን፦

1. የሰይጣንን የማዛል ስልቶቹን መቋቋም አለብን—ዳን. 7፥25።
2. በክርስቶስ ስንኖር፣ የትእግሥቱን ቃል እንጠብቃለን፣ መከራንና ተቃውሞን ለመሸከምም ትእግሥት ይኖረናል—ራእ. 3፥10።
3. በተደሰትነውና በተለማመድነው በክርስቶስ ትእግሥት መታገሥ እንችላለን—2 ተሰ. 3፥5።

**II. ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በሰብዕናው ያስደስታቸውና በመለኮትነቱ ይመግባቸው ዘንድ፣ "እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ" (ራእ. 1፥13) ሊቀ ካህን ነው፦**

ሀ. የሰው ልጅ በሰብዕናው ነው፣ የወርቅ መታጠቂያው መለኮትነቱን ያመለክታል፣ ደረት ደግሞ የፍቅር ምልክት ነው፦

1. ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናትን ለማፍራት ወገቡን ታጥቆ፣ ለመለኮታዊው ሥራ ጠንክሮ ነበር (ዘጸ. 28፥4፤ ዳን. 10፥5)፣ አሁን ግን ደረቱን ታጥቆ በፍቅሩ ያፈራቸውን አብያተ ክርስቲያናትን እየተንከባከበ ነው።
2. የወርቅ መታጠቂያው እንደ መለኮታዊው ጉልበቱ የክርስቶስን መለኮትነት ያመለክታል፣ ደረት ደግሞ አብያተ ክርስቲያናትን ለመመገብ ይህ ወርቃማ ጉልበት የሚንቀሳቀሰው እና የሚነሳሳው በፍቅሩ አማካኝነት እና ከፍቅሩ ጋር እንደሆነ ያመለክታል።

ለ. ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናትን ያስደሰታቸው ዘንድ በሰብዕናው እንደ የሰው ልጅ ይንከባከባቸዋል—ራእ. 1፥13፦

1. የመቅረዙን መብራቶች ተገቢ ለማድረግ ያስተካክላል፣ ደስተኛ፣ አስደሳች እና ምቹ እንሆን ዘንድ ያስደስተናል—ዘጸ. 30፥7፤ ተዛ. መዝ. 42፥5፣ 11፦
   ሀ. የጌታ መገኘት ለእኛ ዕረፍትን፣ ምቾትን፣ ፈውስን፣ መንጻትን እና መበረታታትን በመስጠት ማንነታችንን ለማስደሰት የልስላሴንና በፍቅር የመሞቅን ድባብ ይፈጥርልናል።
   ለ. የሚመግበውን የሕይወትን አቅርቦት እንቀበል ዘንድ በቤተ ክርስቲያን የጌታን መገኘት አስደሳች ድባብ መደሰት እንችላለን—ኤፌ. 5፥29፤ ተዛ. 1 ጢሞ. 4፥6፤ ኤፌ. 4፥11።
2. ማብራታችንን የሚያስተጓጉሉትን አሉታዊ ነገሮች ሁሉ በመቁረጥ የመቅረዙን መብራት ክሮች ይቀረቅማል—ዘጸ. 25፥38፦
   ሀ. የክሩ የተቃጠለው ክፍል፣ የሚጤሰው ክፍል በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት ያልሆኑትን እና መቆረጥ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ሥጋችን፣ ተፈጥሮአዊ ሰዋችን፣ እኔነታችንና አሮጌ ፍጥረታችን ያሉ ነገሮችን ያመለክታል።
   ለ. አብያተ ክርስቲያናት በውስጠ-ነገር፣ በገጽታ እና በመገለጥ አንድ ዓይነት ይሆኑ ዘንድ በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች ሁሉ (ስህተቶችን፣ እጥረቶችን፣ ውድቀቶችንና እንከኖችን) ይቀረቅማል—ተዛ. 1 ቆሮ. 1፥10፤ 2 ቆሮ. 12፥18፤ ፊልጵ. 2፥2።

ሐ. ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናትን ይመግባቸው ዘንድ፣ በደረቱ ላይ ባለው የወርቅ መታጠቂያ እንደተመለከተው ከመለኮታዊ ፍቅሩ ጋር በመለኮትነቱ ይንከባከባቸዋል—ራእ. 1፥13፦

1. ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለመፈጸም ድል-ነሺዎቹ እንሆን ዘንድ በመለኮታዊው ሕይወት እንድናድግና እንድንበስል ሦስት ደረጃዎች ባሉት ሙሉ አገልግሎቱ ሁሉን-እንዳካተተው ክርስቶስ በራሱ ይመግበናል።
2. እንደሚመላለሰው ክርስቶስ፣ የእያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ያውቃል፣ እንደሚናገረው መንፈስ፣ መቅረዞቹን ቀርቅሞ በትኩስ ዘይት፣ በመንፈስ አቅርቦት ይሞላል—2፥1፤ 7።
3. በእንቅስቃሴው እንሳተፍ እና እንክብካቤውን እንደሰት ዘንድ፣ በአብያተ ክርስቲያናት መሆን አለብን።

**III. የጌታ ሰማያዊው ጥንታዊነት ራሱና የራሱ ጠጕር እንደ ነጭ የበግ ጠጕር፣ እንደ በረዶም ነጭ በመሆኑ ታይቷል—1፥14፤ ዳን. 7፥9፤ ኢዮ. 15፥10፤ ተዛ. መኃ. 5፥11።**

**IV. የጌታ ሰባት ዓይኖች፣ ለመመልከት፣ ለማስተዋል፣ ለመመርመር፣ አብርሆት በመስጠት ለመፍረድ እና ለመስረጽ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው—ራእ. 1፥14፤ 5፥6፤ ዳን. 10፥6፦**

ሀ. ሰባት በእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ የመጠናቀቅ ቁጥር ስለሆነ የክርስቶስ ዓይኖች በምድር ላይ ላለው ለእግዚአብሔር እንቅስቃሴና አሠራር ናቸው።

ለ. የጌታ ዓይኖች እንደ እሳት ነበልባል መሆናቸው በዋናነት ለፍርዱ ነው—7፥9-10፤ ራእ. 2፥18፤ 19፥11-12።

**V. የጌታ እግሮች፣ ፍጹም እና ብሩህ የሆነው ምልልሱ መለኮታዊ ፍርዱን ያንቀሳቅስ ዘንድ ብቁ እንደሚያደርገው በማመልከት ልክ በእቶን እንደነጠረ የጋለ ናስ ናቸው—1፥15፤ ሕዝ. 1፥7፤ ዳን. 10፥6።**

**VI. የጌታ ድምፅ ልክ እንደ ብዙ ውኆች ድምፅ ነው (ራእ. 1፥15፤ ተዛ. 14፥2)፣ ይህም ድምፅ በጥብቅነቱ እና በግርማዊነቱ (ተዛ. ራእ. 10፥3) ታላቅ ድምፅ፣ ሁሉን የሚችል የአምላክ ድምፅ ነው (ሕዝ. 1፥24፤ 43፥2)።**

**VII. ክርስቶስ የአብያተ ክርስቲያናትን ብሩህ መልእክተኞች የያዘው ነው—1፥16፣ 20፡-**

ሀ. መልእክተኞቹ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉ መንፈሳዊዎቹ ሰዎች፣ የኢየሱስን ምስክር ኃላፊነት የሚሸከሙት ናቸው።

ለ. እንደ ከዋክብት ሰማያዊ ባሕርይ ያላቸው እና በሰማያዊ ስፍራ ያሉት መልእክተኞች፣ ለሕዝቡ ከጌታ ትኩስ መልእክት ያላቸው ናቸው—2፥1።

ሐ. መሪዎቹ በቀኝ እጁ ውስጥ ስለሆኑ፣ ወደኋላ ማፈግፈግ አያስፈልጋቸውም፤ በእርግጥም ክርስቶስ ለምስክሩ ኃላፊነቱን ይወስዳል።

**VIII. ከክርስቶስ አፍ በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ይወጣል፣ ይህም አሉታዊ ሰዎችንና ነገሮችን ለማደብ የሆነው የሚለየው፣ የሚፈርደው እና የሚያርደው ቃሉ ነው—1፥16፤ ዕብ. 4፥12፤ ኤፌ. 6፥17።**

**IX. የክርስቶስ ፊት መንግሥቱን ለማምጣት ለፍርድ ለሆነው አብርሆት (ራእ. 1፥16፤ 10፥1፤ ማቴ. 17፥2፤ ተዛ. ሚል. 4፥2፤ መሳ. 5፥31፤ ማቴ. 13፥43) ልክ ፀሐይ በኃይሏ እንደምታበራው ያበራል (ዳን. 10፥6)።**

**X. ክርስቶስ፣ *ሥራውን* ሳይጨርስ እንደማይተው የሚያረጋግጥልን ፊተኛውና ኋለኛው፣ አብያተ ክርስቲያናት እንደ አካሉ መገለጥ ሕያው፣ ትኩስ እና ጠንካራ ይሆኑ ዘንድ ሕያዉ ማንነት ነው—ራእ. 1፥17-18።**

**XI. ክርስቶስ የሞት እና የሲኦል መክፈቻ አለው—ቁ. 18።**

ሀ. ሞት ለቃሚ ነው፤ ሲኦል ደግሞ [የተለቀመውን] መሰብሰቢያ ነው፤ ነገር ግን ክርስቶስ ሞትን በመስቀል ሽሯል፣ ሲኦልን ደግሞ በትንሣኤው ድል ነሥቷል—2 ጢሞ. 1፥10፤ ሐዋ. 2፥24።

ለ. እኔነትን ለመካድ፣ መስቀሉን ለመሸከም እና የነፍስ ሕይወታችንን ለማጣት ራሳችንን በማስለመድ ጌታ በመካከላችን ይንቀሳቀስና ይሠራ ዘንድ ስፍራን፣ እድልን እና መንገድን እስከሰጠነው ድረስ፣ ሞትና ሲኦል በቁጥጥሩ ሥር ይሆናሉ—ማቴ. 16፥18፣ 21-26።

*© 2025 Living Stream Ministry*

*© 2025 Living Stream Ministry*